የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፹፮
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፰ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 86
ADDIS ABABA 25th July 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፵፱/፪ሺ፫
የኢትዮጵያ ወጣቶች የስፖርት አካዳሚ ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………ገፅ ፮ሺ፴፱

## CONTENTS

Regulation No. 249/2011
Ethiopian Youth Sports Academy Establishment Council of Ministers Regulation………………… Page 6039

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፱/፪ሺ፫

## የኢትዮጵያ ወጣቶች የስፖርት አካዳሚን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ወጣቶች የስፖርት አካዳሚ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፱/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

፩/ "ኮሚሽን" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፮፻፺፪/፪ሺ፫ የተቋቋመዉ የስፖርት ኮሚሽን ነው፤

፪/ "የአካዳሚክ ሠራተኛ" ማለት በማስተማር፣ በማሰልጠን እና/ወይም በምርምር ሥራ የተሰማራ ሠራተኛ ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 249/2011

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN YOUTH SPORTS ACADEMY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Youth Sports Academy Establishment Council of Ministers Regulation No. 249./2011".

**2. Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Commission" means the Sports Commission established by Proclamation No. 692/2010;

2/ "academic staff" means an employee engaged in teaching, training and/or research activities;

ያንዱ ዋጋ 5.80
Unit price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

፫/ "የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ" ማለት የአስተዳደር፣ የቢዝነስ አመራር፣ የፋይናንስና የሂሳብ ሥራ፣ የአገልግሎቶች አቅርቦት፣ የጥገና፣ የጥበቃና ደህንነት ወይም የመሳሰሉትን ተግባራት የሚያከናውን የአካዳሚው ሠራተኛ ነው፤

፬/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

፭/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፮/ ማንኛዉም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡

፫. **መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ ወጣቶች የስፖርት አካዳሚ (ከዚህ በኋላ "አካዳሚው" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት የስፖርት ትምህርትና ስልጠና ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ አካዳሚው ተጠሪነቱ ለኮሚሽኑ ይሆናል፡፡

፬. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የአካዳሚዉ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸዉም ሥፍራ የማሠልጠኛ ማዕከሎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

፭. **ዓላማዎች**

አካዳሚው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ ለሀገር አቀፍና ለዓለም አቀፍ ውድድሮች በአካልና በአእምሮ ከፍተኛ ብቃት ያላቸዉንና ሥነ-ምግባራቸውን የጠበቀ ምርጥ ወጣት ስፖርተኞች ማፍራት፤

፪/ በተለያዩ የስፖርት መስኮች ለባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤

፫/ ለስፖርቱ ጥራት አስተዋፆ ሊያደርጉ የሚችሉ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች ላይ ማካሄድና የተገኙ ውጤቶችን ማሰራጨት፤

፬/ በሀገር ደረጃ ለተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች የእውቀት ማዕከል ሆኖ ማገልገል፡፡

3/ "administrative support staff" means personnel of the Academy employed to provide administrative, business management, accounting, catering, maintenance, safety, security and such other services;

4/ "region" means any State referred to in sub-article (1) of Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

5/ "person" means a natural or juridical person;

6/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. **Establishment**

1/ The Ethiopian Youth Sports Academy (hereinafter the "Academy") is hereby established as an autonomous federal of sport education and training institution having its own legal personality.

2/ The Academy shall be accountable to the Commission.

4. **Head Office**

The Academy shall have its head office in Addis Ababa and may have training centers elsewhere as may be necessary.

5. **Objectives**

The Academy shall have the following objectives:

1/ to produce physically and mentally competent and ethically sound young sport elites for national and international competitions;

2/ to render capacity building training for professionals in different sport felids;

3/ to conduct research and studies which contribute to the quality of different sport disciplines and disseminate the results thereof;

4/ to serve as a center of excellence for different sport disciplines at the national level.

**፮. የአካዳሚው ስልጣንና ተግባር**

አካዳሚው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የስፖርት ዘርፍ የሙያ ደረጃዎችንና ስልጠና ሥርዓተ ትምህርት የማዘጋጀትና በትምህርት ሚኒስቴር እውቅና ሲያገኝ ተግባራዊ የማድረግ፤

፪/ የክልሎችን፣ የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴንና የብሔራዊ የስፖርት ፌዴሬሽኖችን ፍላጎት እና ዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሰልጣኞችን ምልመላ፣ ቅበላና ስልጠና የማካሄድ፤

፫/ ከክልሎች ታዳጊ ሕፃናትን በመመልመል፣ በመቀበልና በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች በማሰልጠን ለሀገር አቀፍና አለም አቀፍ ውድድሮች በአካላዊ፣ አእምሮአዊና ማህበራዊ ስብዕናቸው ከፍተኛ ብቃትና ተወዳዳሪነት ያላቸውን ምርጥ ወጣት ስፖርተኞች የማፍራትና ስልጠናውን በሚገባ ላጠናቀቁ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፤

፬/ ሠልጣኞች ከስፖርት ስልጠና ጎን ለጎን መደበኛ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉና ውጤታማ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፤

፭/ ሠልጣኞች በሀገሪቱ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማት እንዲሁም የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በተለያዩ መንገዶች እንዲሳተፉ የማስቻል፤

፮/ በሚዘጋጁት የሙያ ደረጃዎች መሰረት በስፖርት አሰልጣኝነት፣ በስፖርት አስተዳደር፣ በስፖርት ሕክምና፣ በስፖርት ሕግና በመሳሰሉት ስፖርት ነክ መስኮች ለባለሙያዎች የአጭር ጊዜና ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን የመስጠትና የብቃት ምዘና ፈተናውን ለሚያልፉ ሰልጣኞች የምስክር ወረቀትና ዲፕሎማ የመስጠት፤

፯/ በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች ምርምር የማካሄድ፤

፰/ በክፍያ ወይም ያለ ክፍያ የማማከርና የስልጠና አገልግሎት የመስጠት፤

**6. Powers and Duties of the Academy**

The Academy shall have the powers and duties to:

1/ develop sports occupational standards and training curriculum and implement same upon accreditation by the Ministry of Education;

2/ recruit, enroll and train trainees based on the demands of the regions, the Ethiopian Olympic Committee and the national sports federations and international best practices;

3/ recruit, enroll and train children from regions and produce highly qualified and competitive young sport-persons who are physically, mentally and socially fit for national and international competitions and award them certificates of competence upon successful completion of their training;

4/ facilitate trainees to continue and become effective in their regular education besides the sport training program;

5/ enable the trainees to participate, in various, in the country's socio-economic development and democratization process;

6/ provide short term and continuing capacity building training according to the established occupational standards in coaching, sport management, sport medicine, sport rules and other sport related fields and award certificates and diplomas for trainees who pass the assessment of competence;

7/ conduct research in different sport disciplines;

8/ provide consultancy and training services with or without charge;

፱/ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የስፖርት ሥልጠናና የምርምር ተቋማትና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሌሎች ተቋማት ጋር ግንኙነት የመመስረት፤

፲/ የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤

1፩/ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን::

፯. <u>የአካዳሚው አቋም</u>

አካዳሚው:-

፩/ የአስተዳደር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ በመንግሥት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ አስፈላጊዉ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል::

፰. <u>የቦርዱ አባላት</u>

፩/ ቦርዱ ሰብሳቢዉን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፤ ቁጥራቸዉም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል::

፪/ የአካዳሚው ዋና ዳይሬክተር ድምፅ የማይ ሰጥ ሆኖ የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል::

፱. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩/ የአካዳሚዉን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤

፪/ የአካዳሚውን የአሰራር መመሪያዎች ያፀ ድቃል፤

፫/ የአካዳሚውን ልዩ ልዩ የአካዳሚክና የምር ምር ክፍሎች አመሰራረትና አሰራር እን ዲሁም የአስፈጻሚ አካላቱን ምደባ ያፀድቃል፤

፬/ የትምህርትና ስልጠና፣ የምርምርና የቴክኖ ሎጂ ሽግግር ሥራዎች የአካዳሚውን ተልዕኮና ዓላማ መሠረት ያደረጉና የዘርፉን ፍላጐት ለማሳካት የሚረዱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፭/ የአካዳሚውን ሰልጣኞች የቅበላ መስፈርት የትምህርት ሚኒስቴርን በማማከር ይወስ ናል፤ በሥራ ላይ እንዲውል መደረጉንም ያረጋግጣል፤



9/ establish relations with the local and foreign sport training and research institutions and other organizations having similar objectives;

10/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

11/ carry out such other related activities as are necessary for the attainment of its objectives.

7. <u>Organization of the Academy</u>

The Academy shall have:

1/ a Management Board (hereinafter the ''Board'');

2/ a Director General and, as may be necessary, Deputy Director Generals, to be appointed by the government; and

3/ the necessary staff.

8. <u>Composition of the Board</u>

1/ Members of the Board, including the Chairperson, shall be designated by the government, and their number shall be determined as may be necessary.

2/ The Director General of the Academy shall be a non-voting member and secretary of the Board.

9. <u>Powers and Duties of the Board</u>

The Board shall have the powers and duties to:

1/ oversee the activities of the Academy;

2/ approve working rules and procedures of th Academy;

3/ approve the establishment and function of th various academic and research units of th Academy, as well as the assignment of the executive officers;

4/ ensure that the educational training, researc and transfer of technology programs are accordance with the mission and objectives the Academy and meet the need of the sector;

5/ approve criteria for the admission of trainees consultation with the Ministry of Educatic and ensure the implementation of same;

፮/ አካዳሚው የሚያስከፍላቸው የአገልግሎት ክፍያዎች እና ያለክፍያ የሚሰጡት አገልግሎቶች በመንግሥት እንዲወሰኑ ለኮሚሽኑ ሃሳብ ያቀርባል፤

፯/ አካዳሚው ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር የትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ጋር የሚያደርጋቸውን ስምምነቶች መርምሮ ያፀድቃል፤

፰/ የአካዳሚውን አርማ ያፀድቃል፤

፱/ በአካዳሚው አካላት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ይወስናል፤

፲/ የአካዳሚው የሥራ ዕቅድና በጀት ለኮሚሽኑ ከመቅረባቸው በፊት ይመረምራል፤

፲፩/ ለኮሚሽኑ የሚቀርቡትን የአካዳሚውን ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች ያፀድቃል፤

፲፪/ የአካዳሚውን የኦዲት ሪፖርት በመመርመር በሪፖርቱ መሠረት አስፈላጊው እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል::

## ፲. የቦርዱ ስብሰባ

፩/ ቦርዱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል::

፪/ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የቦርድ አባላት በማንኛውም ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል::

፫/ የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል::

፬/ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

## ፲፩. የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የአካዳሚው ዋና ስራ አስፈፃሚ ሆኖ ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የአካዳሚውን ስራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል::

6/ submit to the Commission proposals, for government approval, on service fees to be charged and services to be given without charge by the Academy;

7/ examine and approve academic agreements made between the Academy and other local and foreign educational and training institutions;

8/ approve the emblem of the Academy;

9/ examine and decide on appeals against decisions rendered by organs of the Academy;

10/ review the work programs and budgets of the Academy prior to their submission to the Commission;

11/ approve the annual operational and financial reports of the Academy to be submitted to the Commission;

12/ evaluate the audit report of the Academy and ensure that adequate measures are taken in accordance with the report.

## 10. Meetings of the Board

1/ Ordinary meeting of the Board shall be held every three months; provided, however, that an extra-ordinary meeting of the Board may be held at any time whenever called by the Chairperson.

2/ There shall be a quorum when more than half of the members of the Board are present at any meeting.

3/ Decisions of the Board shall be passed by majority vote; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may adopt its own rules of procedure.

## 11. Powers and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Academy and shall, subject to the general directives of the Board, direct and administer the activities of the Academy.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ:-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የአካዳሚውን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፤

ለ) የአካዳሚውን የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የአካዳሚክ ሠራተኞችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የአካዳሚውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ በቦርዱ ከተመከረበት በኋላ ለኮሚሽኑ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለአካዳሚው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

ሠ) የአካዳሚዉን የሥራ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ በቦርዱ ከተመከረበት በኋላ ለኮሚሽኑ ያቀርባል፤

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ አካዳሚውን ይወክላል፤

ሰ) በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለአካዳሚው የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለአካዳሚው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል::

## ፲፪. በጀት

የአካዳሚዉ በጀት በመንግሥት የሚመደብ ይሆናል::

## ፲፫. የሂሳብ መዛግብት

፩/ አካዳሚው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል::

፪/ የአካዳሚው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ::

2/ Without prejudice to the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Academy provided for in Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer the administrative support staff of the Academy in accordance with the federal civil service laws, and the academic staff in accordance with directive approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) prepare and, upon being deliberated on by the Board, submit to the Commission the work program and budget of the Academy and implement same upon approval;

d) effect payment in accordance with the approved work program and budget of the Academy;

e) prepare and, upon being deliberated on by the Board, submit to the Commission the performance and financial reports of the Academy;

f) represent the Academy in all its dealings with third parties;

g) perform such other duties as may be assigned to him by the Board.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Academy to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Academy.

## 12. Budget

The Academy's budget shall be allocated by the government.

## 13. Books of Accounts

1/ The Academy shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Academy shall be audited annually by the Auditor General or by auditors assigned by the Auditor General.

፲፬. **መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ**

ጥሩነሽ ዲባባ ብሔራዊ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል በመባል የሚታወቀው ተቋም መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለአካዳሚዉ ተላልፈዋል::

፲፭. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፰ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

14. **Transfer of Rights and Obligations**

The rights and obligations of the entity known as Tirunesh Dibaba National Athletics Training Center are hereby transferred to the Academy.

15. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa this 25th day of July, 2011

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**